# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፡የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 5 ሰኔ 5 2000 ዓ.ም


## የመለስ መንግስት በጦር ወንጀልና ሰብአዊ ፍጥረት ላይ በተፈጸመ ወንጀል እንደሚጠየቅ የሂውማን ራይት ዋች ዘገባ ጠቆመ።

ተቀማጭነቱ በኒው ዮርክ ከተማ የሆነው አለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት ሂዩማን ራይት ዋች የመለስ መንግስት በጦር ወንጀልና በሰብአዊ ፍጥረት ላይ የፈጸመውና እየፈጸመ ያለው ወንጀል አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን በዘገባው ይፋ አደረገ።አያይዞም ለጋሽ ሀገሮች የመለስ መንግስት በሰብዓዊነት ላይ የሚፈፀማቸውን ወንጀሎችን ለማስቆም መንቀሳቀስ አለባቸው ሲልም አሳስቦአል።

ይህ ጭካኔ የተሞላበት የወታደራዊ ዘመቻ አካል የሆነው ገደብ-የለሽ በደል እየተባባሰ ለሄደው የህዝብ ስቃይ አስተዋጽኦ ያደረገና በሺህ የሚቆጠሩ የክልሉ ነዋሪዎችን ህልውና አደጋ ላይ የጣለ በመሆኑ ድርጊቱ የጦርነት ወቅት ህግጋትን የጣሰና በሰብዓዊነት ላይ ከተፈጸመ ወንጀል የሚቆጠር መሆኑን ሪፖርቱ ገልጿል።

ይህ "የጅምላ ቅጣት፤ በኢትዮጵያ የሱማሌ ክልላዊ መንግስት ኦጋዴን አካባቢ የተካሄዱ ህገወጥ የጦርነት ወቅት ድርጊቶችና በሰብዓዊነት ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች" በሚል ርእስ የወጣው 130 ገጽ ሪፖርት በቻይና ዜጎች በሚካሄደው የነዳጅ ፍለጋ ስራ ቦታ ላይ አማፅያን ላደረሱት ጥቃት አጸፋ የመለስ መንግስት ሰራዊት ከሰኔ 1999 ጀምሮ እያካሄደ ባለው የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ በሲቪሎች ላይ የሚፈጸመው ከልክ ያለፈ በደል እየጨመረ መሄዱን አትቷል።

በተያያዘም አሜሪካ፣ እንግሊዝና ቤልጅየም ይህንን ወንጀል አላየንም አልሰማንም በማለት የተመሳጠሩ ይመስላል ሲሉ አንድ የድርጅቱ ከፍተኛ ተመራማሪ ገልጸዋል።የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ አጥኝዎች ከመቶ በላይ የሆኑ የስቃይ ሰለባዎችን እና የአይን ምስክሮችን፤ እንዲሁም ነጋዴዎችንና የንግድ መሪዎችን፤ በኬንያ፣ በከፊል
ራስገዝ የሰሜን ሱማሌ ምድርና ኢትዮጵያ ያገኟቸውን የክልሉን መንግስት ባለስልጣናት ጭምር አነጋግረዋል። በተጨማሪም፤ መንደሮች በእሳት መቃጠላቸውን የሚያሳይ የሳተላይት ፎቶግራፍ መኖሩ ይህንን በመስከረም እና ታህሳስ 2000 በስፋት የተካሄደውን ጥናት ትክክለኛነት የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል። ፡ወደ ገጽ 4 ዞሯል፤

## መተንፈሱ የማይቀር ተዕቢት መተንፈስ ሊጀምር ነው።

### በመከላከያ ሰራዊቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰ

ሰሞኑን በምስራቁ የአገሪቱ ክፍል በኦጋዴ ነፃ አውጭ ግንባርና እነ መለስ የእኛ ነው በሚሉት የመከላከያ ሃይል መካከል በተካሄደ ከባድ ውጊያ ፤በመከላከያ ሃይል ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱ ተሰማ።

በደገሀቡርና በባቢሌ አውራጃዎች የተካሄደው ይህ ጦርነት በመጠኑም ሆነ በውጤቱ ከእስካሁኖቹ ለየት ያለ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ፤ሁለት ባታሊዮን የሚያህል የመከላከያ ሃይል መደምሰሱና በመቶዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች መማረካቸው ላለም አቀፍ ዜና አውታሮች ይፋ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል። ፡ወደ ገጽ 4 ዞሯል፤

### መለሰ ሀገር ሲሸጥ፣አዜብ በውጭ ሃገራት ሃብት ማከማቸቱን ተያይዛዋለች።

ለግንቦት 7 ቅርበት ካላቸው ምንጮች በደረሰን ዘገባ መሰረት የጠቅላይ ሚንስትሩ ባለቤት አዜብ መስፍን በገልፍ ሃገራት የሪል ስቴት፣ህንጻ ግዢና ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ዝውውር እንደምታደርግ ታውቋል።አዜብ መስፍን በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ቢሪይ የተባለ የሪል ስቴት ካምታኒ እንደምታንቀሳቅስ ለማወቅ ተችሎአል።ዱባይ ከተማ በሚገኘው የቀድሞ የወያኔ የባህል ክፍል ሃላፊ እያሱ በርሄ አማካይነት ይህን የህንጻ ግዢና፣ ወደ ገጽ 2ዞሯል፤

### መለስ አዜብን በመጠቀም ጀነራሎቹን መደለሉን ተያይዞታል።

ከዚህ ቀደም ከምታደርገው በተስፋፋ መልኩ የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን በመከላከያ ጀነራሎች ቤት ለቤት እየዞረች መደለሏንና መሸንገሉን እንደቀጠለች ተነገረ።በየጀነራሎቹ ቤት መሄድ ያዘወተረችው አዜብ በተለያየ ስበብ አስባብ ለቤተሰቦቻቸው ገንዘብ መስጠት ያበዛች ሲሆን፣ በተለይ አዛኝ በመምሰል የቤት ቁሳቁሳቸውን እንዲቀይሩ ገንዘብ መስጠቱን ባለፈው ሰሞን ማስፋፋቷ ለማወቅ ተችሏል። ፡ወደ ገጽ 4 ዞሯል፤

## የማን መንግስት ነው የሚመራን?

### በእርግጥ ይህ መንግስት የእኛ ነውን?

ከይኩኑ አምላክ

አብዛኛዎቹ የአለማችን የስነ-መንግስት ሊቃውንት ለአንድ ማህበረሰብ መንግስት ለምን ያስፈልጋል በሚል ጥያቄ ዙሪያ ሰፊ ምርምር አካሂደዋል።በዚህ ምርምር ሂደት ብዙዎቹን የሚያስማማ የጋራ ነጥብ ቢኖር ለአንድ ማህበረሰብ የመንግስትን አስፈላጊነት ከሚያጎሉ አንኳር ጉዳዮች መሃከል በሃገር ውስጥ በህብረተሰቡ መሃከል ህግና ፍትህን ማስፈን ሲጠበቅበት፣ከሃገር ውጭ ሊሰነዘሩ ከሚችሉ ጥቃቶች ህብረተሰቡን መከላከል ያለና የሚኖር መንግስት የተሰኘው ተቋም ሃላፊነት እንደሆነ ነው።እነዚሁ ተመራማሪዎች አክለው መንግስት እነዚህን ሁሉ ሃላፊነቶቹን የሚወጣው በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከህብረተሰቡ በሚያገኘው እንደ ግብር፣የጉልበትና የህይዎት መስተዋጽ እንደሆነ በስፋት ይስማማሉ።
ይህ ቀኖናዊ የሆነ ግዛትንና የወሰን ድንበርን የማስከበር ሃላፊነት በስልጣን ላይ ያሉ መንግስታት አምባገነን፣ፈላጭ ቆራጭ ፣ዴሞክራት ወይም ሌላ የተለየ ባህሪያት- መንግስት ኖራቸውም አልኖራቸውም ለጥያቄና ለድርደር የማይቀርብ ጉዳይ ነበር፣ነውም።በታሪክ እንደምናየው ብዙ አምባገነንና ፈላጭ ቆራጭ ስርአቶች ህዝባቸውን በአስተዳደር ቢበድሉ፣ፍትህና ርትህ ቢያዛቡ፣እንከነ ብዙ ቢሆኑም የግዛት ሉአላዊነትን ጉዳይ በተመለከተ የተለሳለሰ አቋም የወሰዱበት ወቅት አልተዘገበም።እንዳውም በአለም አቀፍ ተቋማትና ህግጋት ጉልበት ማግኘት እየቀነሰ ቢመጣም ብዙ የአለማችን መንግስታት በጠነከሩና ባበጡ ቁጥር ከግዛታቸው አልፈው ማስፋፋት፣በአካባቢያቸው ከዛም አልፈው የአለም ልእለ ሃያል የመሆን ዝንባሌ ባለንበት ዘመናዊ አለም ሳይቀር ያልተተወ፣ብዙ መንግስታት በውስጣቸው አልመው የሚንቀሳቀሱበት ጉዳይ ነው። ፡ወደ ገጽ 3 ዞሯል፤

# ርእሰ አንቀጽ

## የሰኔ አንድን ሰማእታት 3ኛ አመት ስንዘክር

ስለ ሙታን ሰማእታት ባናነሳ ደስ ባለን ነበር :: ኢትዮጵያችን ሙታንን የመዘከር የታሪኩዋን ዳራ አልፋ ልደትንና ህይወትን ፤ ሳይንስንና ምጥቀትን ፤ ሃብትንና መንፈሳዊ ዕርገትን ልታከብር ብትችል ምንኛ ደስ ባለን ነበር:: አለመታደል ሆኖ ወደፊት ለመመንጠቅ ባኮበኮብን ቁጥር፤ ቅልጥማችንን ሰብሮ ባለንበት መርጋት ብቻ ሳይሆን ተንከባለንም ወደኋላ እንድንቀር የሚያሰገድዱን ሃይላት ዛሬም እንደሰለጠኑብን ይገኛሉ :: በግንቦት 97ም ያኮበኮበችው ንስረ ኢትዮጵያ ክንፏ ተሰብሮ ከተሽመደመደች እነሆ ሶስት አመታት ተቆጠሩ:: ንስረ ኢትዮጵያን ማን ሰበራት? ለምንስ ሰበራት? እንዴትስ ሊሰብራት ቻለ? ሰባሪው ለምንስ ተፈቀደለት? ጥያቄዎቹ ብዙ ናቸው:: የጠራ መልስም ይሻሉ:: ለሰማዕታቱም እዳችንን የምናወራርደው በእንባ ሳይሆን፤ እነዚህን ጥያቄዎች በተገቢው ስንጠይቅና ስንመልስ፤ በመልሳችንም ላይ ተመሥርተን ለተግባር ስንተጋ ብቻ ነው ::

የሰኔ 1 ቀን ጭፍጨፋ የተካሄደው መለስ በህዝብ ድምፅ በተረታ በሶስተኛው ሳምንት ነበር:: ዝም ብሎ የምርጫውን ውጤት ያለገደብ መጠበቅ የደከማቸው ዜጎች «የተሰ ረቀው ድምፃችን ይመለስ» ብለው ወደ አደባባይ በመትመማቸው አገዛዙ ከፍርሃቱም ከጥጋቡም በተደባለቀ ምላሽ የአጋዚ ነብሰ በላዎችን በሰልፈኛው ላይ ስላሰማራበት የደ ረሰ እልቂት ነበር :: የሙታኑ ቁጥር እስከዛሬም አይታወቅም :: ያለ መሪ ድርጅት ፤ ያለምንም አቀናባሪ በየሰፈሩ የተመመው ሰልፈኛ በአቅራቢ መነፅር አነጣጥረው በሚተኩሱ አግአዛውያን ያለርህራሄ ተጨፈጨፈ:: ግድያው በግንቦት 1969 ደርጉ በሜይ ዴይ ሰልፈኛ ላይ ከደረገው ጋር ተመጣጣኝ ሲሆን ፤ የወጣቱ ወኔና ቆራጥነት ግን የ69ኞቹን ታላቅ ወንድሞቹን አርበኝነት ያስከነዳ ነበር :: ልዩነቱ የ69 ተቃውሞ የተደራጀ ሲሆን የ97ቱ ግን የስርአቱ ጥጋብና ብልግና ያስመረረው ወጣት በተናጠል ተጋድሎውን ያሳየበት የጀግንነት አውድማ ነበር:: ያለተስፋ ፤ ያለሥራ ፤ ያለአለኝታ፣ በሰገራ መፍሰሻ ቱቦ ውስጥ ከሚኖር አይጥ ህይወት ባልተ ሻለ የሚኖረው ወጣት፤ በእብሪት የሚደፈጠጥ ትል አለመሆኑን ለራሱም ለአለሙም ለማረጋገጥ፤ ሰብእናውን ከወደቀበት ፈልጎ አግኝቶ ፤ ለለውጥ ከተሰው የአለም ጀግኖች ተርታ ስሙን ለማስመዝገብ ያደረገው እሽቅድምድም ስለነበር፤ ይበል ፤ ይደገም የሚሰኝ ነው:: ከሰብእናዬ የሚመነጩ ተፈጥሮአዊ መብቶች አሉኝ ብሎ የተነሳ ጀግና ነበርና አበጀህ ልንለው ይገባል:: እንደ ከብት እንደ እንስሳ በረሃብ እየተንጠራወዘ ከመሞት፤ «በሃገሬ አደባባይ በአለም ጉባኤ ፊት የእርዳታ ንፍሮ እያሻመደ በዝግታ የሞተ ሳይሆን፤ ለመብቱ ቀናኢ ሆኖ ከግፈኞች ጋር እየተናነቀ ሞተ» ተሰኝቶ ታሪኩን ሊያስነብብ የቆረጠ ጀግና ስለነበር ሊወደስ ተገቢ እንጂ ነው :: አርነት የወጡ የአለም ህዝቦች ሁሉ ከዚህ በተለየ መንገድ ሄደው ያገኙት ነፃነት ከቶ አልታየምና ::

የመለስ አገዛዝ ብሄራዊ ጥቅም የሚባል ጉዳይ ሊገባው የማይችል፤ የራሱ የፖለቲካ ሥልጣን ከሃገር በላይም ተመራጭና ውድ አድርጎ የሚያይ መወገድም የሚገባው ሥርአት በመሆኑ ነው የሰኔ 1ን ጀግና ሞትን እንዲዳፈር ያተጋው:: ህዝቡ የስርአቱ መወገድን አስፈላጊነት አምኖ በሰላም እንዲገለል ለማድረግ፤ በግንቦት 7 ቀን 1997 ምርጫው ፍላጎቱን ግልፅ ያደረገ ቢሆንም፤ የዛሬ ሶስት አመት በሰኔ 1 ቀን የንፁሃንን ደም በማፍሰስ የህዝቡን ድምፅ ለመቀልበስ መለስ የጀመረው እመቃ በሙሉ ሀይሉ እንደቀጠለ ነው:: ይህ ብካይ በአፋጣኝ እንዲቆም ማድረግ የሰኔ 1 ሰማእታት ለቀረነው ዜጎች ያስረከቡት እዳ ነው:: ይህ እዳ የወጣቱ፣ የሽማግሌው፣ የሴቱ፣ የወንዱ፣ የገበሬው፣ የላብ አደሩ፣ የተማሪው፣ የአስተማሪው፣ የነጋዴው፣ የባለፋብሪካው፣ የባለሃብቱና የባለእውቀቱ እዳ ነው:: ለሁሉም አይነት ትግል ለሁሉም አይነት መስዋእትነት ቆርጦ በመነሳት ብቻ የሚያወራርዱት እዳ ነው::

አልረሳነውም ይህ እዳ የወታደሩም እዳ ነው:: የመለስ አገዛዝ የአመፅ ክንድ በመሆን ያገለገለው የመከላከያ ሃይል ከስህተቱ ተምሮ የግፈኞች የአመፅ ክንድ አልሆንም ብሎ በማያንገራግር ቃልና ቆራጥነት ከህዝብ ጎን በመቆም በደርጊት በሚገለጽ ንስሃ ሊያወራርደው የሚገባ እዳ ነው:: በወገኑ የዴሞክራሲያዊ መብት እመቃ ላይ እንዲዘምት የተደረገ፤ ዋነኛው ስራው በሆነው በሃገር ግዛታዊ አንድነትና ሉአላዊነት ላይ ተገዶ ዝምታን እንዲመርጥ የተደረገ የመከላከያ ሃይል፣ እስከ መቼ በሃገሩና በራሱ መጻኢ ህልውና ላይ ከፍተኛ መዘዝ በሚስከትል የመለስ ዜናዊ ወንጀል ተባባሪ ሆኖ ይቀጥላል ? አይመስለንም ደግሞም አይገባምም እንላለን:: ጠብመንጃውን ምንሊክ ቤተመንግስት ውስጥ ወደጎለታቸው ከሀዲዎች ማዞር ይጠበቅበታል:: ከሃገር አታጣሉን፤ ከዘመድ አትነጥሉን፤ ከወገን አትለያዩን፤ የምንቆመው ለህገ መንግስቱ እንጂ ለማንም ወሮበላ ከሃዲ አይደለም ሊል ይገባል:: ሁሌም ባለነፍጡ በአገዛዙ ላይ መሳሪያውን የሚያነሳው ህዝብ ለመብቱ ሲተጋ መሆኑን አውቆ፤ የኢትዮጵያም ህዝብ በአንድ በኩል ወታደር ልጆቹ ከግፍ እንዲቆጠቡ፤ ከአገዛዙ እንዲነጠሉ እየመከረ፤ በሌላ በኩል ግን ማለቂያ ከሌለው ትእግስቱ ጋር ወደር የሌለው ሃገራዊ ፍቅሩን ደርቦ፤ «ለትእግስትም ወሰን አለው» ብሎ መብቱን ከገዢዎቹ መንጋጋ ፈልቅቆ ሊወስድ ይገባል::

<u>**መተንፈሱ የማይቀር**</u> ከገጽ 1 የዞረ

እንዲሁም በርካታ የመከላከያ ሃይል ተሸከርካሪዎች መማረካቸውን የገለፁት የአማፅያኑ አመራሮች፣በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ የተማረኩትን ወታደሮች በአለማቀፍ መገናኛ ብዙሀን አማካይነት ይፋ እንደሚያደርጉ አሳውቀዋል።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ መንግስት ጦር የሚደገፈው የሶማሊያ የሽግግር መንግስት _በሶማሊያ ዳግም የነፃነት ሀይላት ክፉኛ መመታቱና እየተሸነፈ መምጣቱ ታወቀ።

በስፍራው የሚገኙ የ አለማቀፍ ዜና አውታር ጋዜጠኞች እንደዘገቡት፣የዳግም ነፃነት ሀይላቱ -- በሽግግር መንግስቱ ላይ ከፍተኛ ድል እና የበላይነትን እየተቀዳጁ ነው።

“በቅርቡ ባይደዋ በ አማፅያኑ ቁጥጥር ስር ልትወድቅ ትችላለች ይባላል”ተብለው የተጠየቁት የሽግግር መንግስቱ ባለሙዋሎች፣”እኛ አንዋጋም”በማለት ሽንፈታቸውን ለማስተባበል እንኳዋ አልደፈሩም። ይህም ለመለስ መንግስት ከፍተኛ ሽንፈትና ኪሳራ እንደሆነ በአለማቀፍ ሚዲያዎች እየተዘገበ ባለበት ባሁኑ ወቅት፣ይህንኑ ተከትሎ በመለስ የጦር መኮንኖችና_በገዥው ፓርቲ አመራሮች መካከል ሽኩቻና አለመተማመን መንገሱ ታውቂዋል።

አቶ መለስና አማካሪያቸው አቶ በረከት በኢትዮጵያ ጦር የደገፈው የሶማሊያ የሽግግር መንግስት በማያዳግም ሁኔታ አማፅያኑን ስለመደምሰሱ እንዲሁም የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር ጨርሶ ስለመጥፋቱ በተደጋጋሚ ሲናገሩ መቆየታቸው ይታወሳል።

<u>**መለሰ ሀገር ሲሸጥ፣አዜብ**</u> ከገጽ 1 የዞረ

ችለናል።በአሁኑ ወቅት በዱባይ ሃገር ሳርያህ በተባለው ስፍራ ሊድርስ ሊንክ ትሬዲንግ የተባለ ካምፓኒ በባለቤትነት የሚያንቀሳቅሰው እያሱ በርሄ ዋነኛ ስራው ይህን ከአዜብ መስፍን ጋር ግንኙነት ያላቸውን የገንዘብና ንብረት ነክ ጉዳዮች ላይ መስራት እንደሆነ ከስፍራው ለመረዳት ችለናል።

የህዝብ ንብረት ከሆነው የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ተቋም መስመር በመስረቅ በድብቅ ወደውጭ ሀገራት ስልክ በማስደወል በጥቂት ጊዜ ከሚሊየነሮች ተርታ የተመደበው እያሱ፣ወንጀሉ ተደርሶበት በሙስና ክስ ማረሚያ ቤት ቢታሰርም እሰካሁን ግልጽ ባልሆነ ምክንያት እስሩን ሳይጨርስ በመንግስት ጣልቃ ገብነት በህክምና ሰበብ ከሃገር እንዲወጣ ተደርጎ፣ ከዛም ክሱ መቋረጡ ይታወቃል።በእስር በነበረበት ወቅት በመንግስት ወጭ በ15 ሺህ ዶላር ክፍያ ከኦፕን ዩኒቨርሲቲ መለስ ዜናዊን ጨምሮ የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣናት ያገኙትን የኤም ቢ.ኤ ዲግሪ ባለቤት ሆኖአል።ነገር ግን በወቅቱ ትምህርቱን ቢጨርስም ከፓርቲው ጋር ባለው ጠብ የተነሳ መዝሙር ፈንቴ የተባለው የብአዴን አመራር ዲግሪውን እንዳያገኝ ተደርጎ እያሱ ሳይማር ያውም በእስር ቤት የኤም ቢ.ኤ ዲግሪ ባለቤት መደረጉ በስርአቱ አናት ሳይቀር ያለውን መድሎ የሚያሳይ እንደሆነ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

እያሱ በርሄ ጫካ በነበሩበት ወቅት የባህል ክፍሉን ሲመራ በውጭ ሀገራት ከህዝብ በየመድረኩ የሚሰበሰበውን ብዙህ ሺህ ገንዘብ ወደግል ኪሱ እንደሚከት፣በዚህም በህወሃት ውስጥ ጥቂት ከሚባሉ ባለ ገንዘቦች አንዱ እንደነበር ታውቋል።ስልጣን ከተያዘ በኋላም ከባለስልጣኖቹ ጋር ባለው ቀረቤታ ለባለሃብቶች ጉዳይ በማስጨረስ ጉቦ አቀባባይ እንደነበር ይነገራል። ፡

**አዘጋጆች**
ፋሲል የኔአለምና እና ደረጀ ሃ/ወልድ
የቀድሞ የአዲስ ዜና እና የነጻነት ጋዜጣ አዘጋጆች

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር**
POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

**የግንቦት ሰባት ድምጽ ጋዜጣ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፡ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ አቶ መሰፍን አማን፣አቶ ቸኮል ጌታሁን፣ሁሉም የቅንጅት ለአንድነትና ዴ ሞክራሲ ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት የነበሩ፡፡

## የማን መንግስት ነው የሚመራን?

ከገጽ 1የዞረ

ህዝብን ለማስተዳደር የመንግስትን ሃላፊነት የሚወስዱ ግለሰቦችና ቡድኖች ከሁሉ አስቀድመው መፈጸምና ማስፈጸም ያለባቸው ተግባር ድንበርን ማስከበር፣በሉአላዊነት ላይ ጥቃት ሲሰነዘር ህዝቡን በማስተባበር አርአያ ሆኖ መስዋእትነትን በመክፈል ሀገር ለትውልድ ማስተላለፍ ነው።

በ1648ዓም የዘመናዊ ሃገራትን መመስረት ይፋ ካደረገው የዌስተፋሊያው ስምምነት ሆነ ከዛ ወዲህ ውል ተደርጎባችው ተግባር ላይ በዋሉ አለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስምምነቶች በአንድ ሃገር ወሰንና የሉአላዊነት መገለጫ በሆኑ ነገሮች ላይ ጥቃት ሲሰነዘር መንግስት የተባለው ተቋም የሚወስደው የአጸፋ እርምጃ፣ማለትም ወሰኑን በሃይልም ጭምር ለማስከበር የሚገባበት ጦርነትም ቢሆን ፍትሃዊ ተደርጎ ይወሰዳል።ስለ ጦርነት አስፈላጊነት እየደሰኮርኩ እንዳይደል ተረዱልኝ፣ሃሳቤ እንዳው አንድ መንግስት ቢያጣ፣ቢቸገር፣ቢፈልጥ፣ቢቆርጥ ወሰኑን ለመጠበቅ፣ለመከላከል ከተቻለም ለማስፋት ሲሰራ እንጂ፣ አሁን በሃገራችን እየተፈጸመ እንዳለው ተግባር ሲፈጸም ስላልሰማሁ እንጂ።ባለኝ የታሪክና የፖለቲካ እውቀት በየትኛውም የአለም ክፍል የገዛ ሀገሩን ግዛት አስረክቦ፣ለሌላኛው ሃገር የግዛት ይገባኛል መብት ጥያቄ ተገቢነት በገዛ ሃገሩ ፓርላማ ፊት ቀርቦ የተከራከረ መሪ ቀርቶ ተራ ዜጋ አላውቅም።በአንድ መስክ በዛሬዋ አለማችን የታደሉት ሃገራት በምጣኔ ሃብት፣በቴክኖሎጂ፣በወታደራዊና ፖለቲካ መስክ ፈርጥመው ከሃገራቸው አልፈው የአካባቢያቸው፣ከዛም ባሻገር የአለም ሃያል ለመሆን በርትተው በሚሰሩበት ወቅት፣በሌላው መልክ ያልታደልን ኢትዮጵያውያን እድሜ ለነመለስ መንግስት ባለቤት የሌለው ሃገር ያገኙ እስኪመስል፡በመስዋእትነት የተረከብነውን ወሰን በየጊዜው ለጠየቀ በማደል ላይ ይገኛሉ።የመንግስት አስፈላጊነትና ምንነት ትርጉሙ እስኪጠፋ ድረስ የህዝቡን ምግብ ፍላጎት አለማሟላት ተስኖአቸው ዳግም በልመና ስማችንን ማስጠራት ሳያንሳቸው፣ለዘመናት በፍቅርና አንደነት ተቻችሎ የኖረን ህዝብ በፈጠሩት ጎሳ ተኮር ፖለቲካ ደም ማቃባት አልበቃ ብሎአቸው፣እንኳን መውረር እራሱን ከሳምንት በላይ መከላከል ያልቻለን ሃይል ሊወረን አስቧል በሚል ሰበብ በሰው ሃገር የውክልና ጦርነት በመክፈት የወታደሮቻችን ሙት አካል በሞቃዲሹ ጎዳናዎች ሲጎተት በየአለሙ የቴሌቪዥን መስኮት አይተን ማፈራችን ሳይገታቸው፣እነሆ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ድፍረት ለሌላ ሃገር የድንበር ይገባኛል ጥያቄ ሽንጥ ገትረው የሚከራከሩበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል።እንዳንድ ጊዚ ጥፋቱን ሁሉ ከነሱ ላይ አወርድና እነሱስ ምን ያድርጉ እኛ ዝም አልናቸው፣ የሚል መልስ ለራሴ እሰጣለሁ።ምንድነው የሚባለው ከነተረቱ" ፈሪ ሲገኝ እኔን አያርገኝ" አይደል፣ነገሩስ እንዲያ ይመስላል።

እስቲ አስቡት፣ሁለት አስርታትን ሊደፍን ስሉስ አመታት የቀሩት የአቶ መለስና አባሪዎቻቸው መንግስት በሌሎች መስኮች ያስመዘገባቸውን የምጣኔ-ሃብት፣የፖለቲካና ሌሎች የፖሊሲ ግድፈቶች ለጊዜው ወደጎን እንተው ብንል እንኳ፣የድንበርን የግዛት ሉአላዊነትን ብሎም ብሄራዊ ጥቅምን ለድርድር ማቅረብ ሳይሆን እንዳልነበር በማድረግ የሰሯቸውን መሰረታዊ የሚባሉ የፖሊሲ ስህተቶችን ስንመለከት፣ኢትዮጵያዊ በሆነ ሰው አእምሮ የሚመጣ አንድ ጉልህ ጥያቄ ይኖራል፤እርሱም በእርግጥ ይህ መንግስት የእኛ ነውን?።የዚህን ጥያቄ ፍትሃዊነት ለማስረገጥ ስልጣን በያዘ ማግስት የሉአላዊነት መገላጫ ስንደቅን በማንኳጠጥ የጀመረውን ክህደት፣ ከገዛ ግዛቱ የምትለይ ክልልን እውቅና ስጡልኝ ብሎ ቀዳሚ ሆኖ ሌሎችን ማበረታታቱ አለምን አስደምሞ አገርን አብሽቆ ሃገሪቷን የአለም ታላቋ ወደብ አልባ በማድረግ ሳይበቃው፣እሺ ጦርነት ይቁም እንጂ በሰላም አብሮ በመኖር ሁሉንም እናገኘዋለን ባልን አንድ አስርትም ሳይሞላን በተወረርን ጥሪ ፣ሀገር ተንቀሳቅሶ መቶ ሺህና ከዛም በላይ ወጣት ደም ፈሶ፣አጥንት ተከስክሶ፣ምድሩ በታንክ ታርሶ ተገኘ የተባለው ድል በዳግም ክህደት ተለውሶ በእነ መለስ ሸፍጥ መሬታችን ተወርሶ አረፍነው።

ማፈርንና ከእፍረት ጋር የማይተዋወቁት የዛሬ ገዢዎቻችን ጥቂት ሰንብቶ ሊታወቅ ፍርድ ቤቱ ከጠየቅነው በላይ ሰጥቶናል አበሳውን እያበሉት ያለን ህዝብ ይህም አልበቃ በሎአቸው በቅጥፈት አታለው በአደባባይ አስጨፈሩት።ተረቱን ላክልና "ሃገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል" የሚል አባባል በሃገራችን ያለ ይመስለኛል፣እንደኔ እንደኔ የገባንበት ዝምታ ልበለው ፍርሃት ከዚህም ባላይ አለማስከተሉ ነው የሚገርመኝ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ዛሬ ሁላችንም እራሳችንን ቆም ብለን መጠየቅ ያለብን አንድ ነገር ያለ ይመስለኛል፣የትእግስት ወሰኑ የት ነው፣የጨዋነት ልኩ፣ይሉኝታችንስ ምን አተረፈልን የትስ ያደርሰናል?።ይህን የምለው እምሃበ-አልቦ አይደለምና ምክንያቱም፣ለመለስና አጋሮቹ የእኛ ትእግስት የታየው ከፍራቻ እንጂ፣ይሉኝታችን ጨዋነታችን እንደሞኝነት እንደ ድክመት መወሰዳቸውን በሰሞኑ ዳግም የክህደት ተግባራቸው በመታዘቤ ነው።አጋነንክ ካልተባልኩ በስተቀር አንድ ህዝብ በገዛ መሪ ተብየዎቹ ሲዋረድ ቅጥ ባጣ መልኩ የክብሩ፣የህልውናውና የማንነቱ መገለጫ የሆኑ እንደ ሰንደቅ አላማ፣የግዛት አንድነትና ወሰን ሲብጠለጠሉና ሲሸቀጡ ከማየት የበለጠ፣ መዋረድን ምን ሊገልጸው እንደሚችል አላውቅም።የሱዳኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ፕሬዚዳንት ሳይሆን የኢትዮጵያው ርእሰ-መንግስት የሆነው ጠቅላይ ሚኒስትር በገዛ ፓርላማው ቀርቦ የሱዳን የመሬት ይገባኛል ተገቢነት አለው፣ገበሬዎቻችን የሰው መሬት ወረው አስፋፍተዋል፣ስለዚህ ሰሞኑን ሱዳን የወሰደችው የማፈናቀል እርምጃ ተገቢ ነው የሚል ልፈፋውን ማሰማቱን ላየ ነገሩ ግራ መሆኑ አይቀሬ ነው።በሃገራችንና ወዳጅ በሆነው በሱዳን ህዝብ መሃል ግጭት ተፈጥሮ የማየት ፍላጎት የለኝም፣ነገር ግን ሰሞኑን በተፈጠረው ሁኔታ መንስኤነት ለሚከሰት ማንኛውም ጥፋትም ሆነ ጉዳት ከሁሉም በላይ መለስና የሚመራው አስተዳደር ግንባር ቀደም ተጠያቂ ናቸው እላለሁ።ነገሩን በሃቅ ካየነው የሱዳን መንግስት በበኩሉ የቀረበለትን የመሬት ስጦታ ከመቀበል የሚያፈገፍግ ሞኝም እንዳይደለ መታወቅ አለበት።"ማን ሞኝ አለ.." አይደል አባባሉ።በሰሞኑ የዜና ዘገባዎች ሪፖርት መሰረት ተላልፈው የተስጡት መሬቶች እምቅ የነዳጅ ክምችት ይኖርባቸዋል የተባለው በራሱ አንድ ጠቋሚ ነገር ያለ ይመስላል።

የዛሬ መቶ አመት የሩሲያ ዛር የአላስካ ግዛት ጥቅም የለሽ መስሎት ጥቂት በሚባል ገንዘብ ለአሜሪካ መንግስት መሸጡ የግዛቱን የእምቅ ከርሰ ምድር ዘይት ባለቤትነት ሲመለከቱ በዛሬ የሩሲያ ትውልዶች ዘንድ የሚፈጠረው ቁጭት ቀላል እንዳማይሆን መገመት ይቻላል።ዛሬ በገዢዎቻችን ስለሚፈጸመውና ስላለነው እኛ የነገዎቻችን የሚሰማቸውን ስሜት ማሰቡ ራሱ ሌላ የራስ ምታት ይፈጥርብኛል።

የእኛም ዝምታ፣የነመለስም እብሪት በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ፣ከትላንት በስቲያ ሃገር ቆርሶ ወደብ አልባ ሲያደርገን በዝምታችን እዳላለፍነው፣ትላንት በመስዋእትነት የተገኘውን የባድመ ድል ፍሬ ሲያስነጥቅ በምን ይደረጋል እንዳልተውነው፣ዛሬ የጎረቤት ጠበቃ ሆኖ የሰው መሬት ወረናል በምእራብ በኩል መሬት ሰጥተናል ብሎ አይን አውጥቶ ሲሞግተን ያንኑ ዝምታችንን ከመረጥን፣ ነገ ከነገ ወዲያ የአዲስ አበባን ዳርቻዎች፣የእንጦጦን ጋራዎች ለጠየቀ ጎረቤት ሃገር ከመስጠት የሚያግደው የህሊና፣የህግ፣የሃይልና ሌላም ሃይ ባይ ገደብ እንደሌለው ልናውቅ ይገባል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ነን የምንል ለሃገራችን በጊዜው ልንደርስላት ካልቻልን፣በዚህ አካሄድ ሃገራችንን እንደ ሳሙና አሟምተው ከመጨረስ ወደኋላ እንደማይመለሱ ለመገመት ብዙ መራቀቅን አይጠይቅም።የከዚህ ቀደሙ የመለስ መንግስትን ድርጊት ለተመለከተ ከትላንት በስቲያ፣ትላንትና ዛሬ እንዳደረገው መንግስት ከሚባል ተቋም የማይጠበቅ ድርጊት ማስቆም ካልቻልን ቀሪውን የሃገራችንን ክፍል ማስታወቂያ አውጥቶ፣ ከተገኘ በጅምላ ካልሆነ በጭርቻሮ ግልጽ ሽያጭ ከመቸብቸብ ወደኋላ እንደማይል መገንዘብ አለብን።፡ *ወደ ገጽ 4 ይመልከቱ*

## <u>የማን መንግስት ነው የሚመራን? ከገጽ 3የዞረ</u>

ለማጠቃለል የመለስ መንግስት የሃገር ክህደት የተለመደ አባዜ ከግዜ ወደግዜ ሲብስ እንጂ ሲሻሻል አልታየም።ህዝብ የሚጠብቅበትን ሃገርን የመከላከል ከባድ ሃላፊነት መወጣቱ ይቅርና የሃገር ሉአላዊነትን አደጋ ውስጥ መክተት የዘወትር ተግባር አድርታል።ህዝብ በህግ የመተዳደር፣በመንግስት የመመራት፣ስርአት የማክበር ግዴታ እንዳለበት ሁሉ የህልውናው መገለጫ የማንነት ክብሩ ማረጋገጫ የሆኑ እንደ ሰንደቅ አላማ፣ወሰንና ድንበር በገዛ ራሱ መንግስት አደጋ ላይ ሲጣሉ በራሱ መንገድ የራሱን ህዝባዊ እርምጃ መውሰድ መብት እንዳለው ሊሰመርበት ይገባል።ቀደምቶቻችን በመስዋእትነት ዋጋ ከፍለው ያቆዩልንን ሃገር ለተተኪ ወራሾቻችን ሳትሸራረፍ የማስረከብ ታሪካዊ ግዴታም አለብን።በእርግጥ ትግሉን የሚያከብደው ከሃገር በቀል ከሃዲ ጋር መሆኑ እሙን ነው።ነገር ግን የክህደት ጉዞውን ዛሬ ማስቆም የሌላ ሳይሆን የእያንዳንዳችን ሃላፊነት ነው።በዚህ አባባል ጽሁፌን ልደምድም፣በአንድ ወቅት ነው አሉ እንዲህ የተባለው፤-

ስወጣም አዝየ፣ስገባም አዝየ
ጀርባየ ተላጠ፣ናውረድ ሰውየ

ቀልድ የለም ለችግሮቻችን ሁሉ መፍትሄ ያለው በዚህ መንገድ ስንታገል ብቻና ብቻ ነው።

## <u>የመለስ መንግስት በጦር ወንጀልና ሰብአዊ ፍጥረት ላይ በተፈጸመ ወንጀል እንደሚጠየቅ የሂውማን ራይት ዋች ዘገባ ጠቆመ።</u>

ከገጽ 1 የዞረ

በሚዘገንን ሁኔታ ሰዎች በምሽት በጠመንጃ ሰደፍ ሲደበደቡ፤ በአደባባይ ግድያ ሲፈጸም እንደነበርና እንዲሁም መንደሮች በእሳት እንደጋዩ የጥቃቱ ሰለባዎችና ምስክሮች ለሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ገልጸዋል።

የወታደራዊ ጥቃቱን ርምጃ ተጋግሎ በነበረበት ከጁን እስከ መስከረም 2000 የመለስ መንግስት ሰራዊት ጠቅላላውን የገጠር ህብረተሰብ ከስፍራቸው በማስለቀቅ በርካታ የገጠር መንደሮችን እንዳወደመ፤ በዚያውም በሽማቂዎች ደጋፊነት የተጠረጠሩ ግለሰቦችን ለሌሎች ምሳሌ ይሆናሉ በማለት ቢያንስ 150 ያህል ሲቪሎችን እንደረሸነ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሲቪሎችን በዘፈቀደ ከወታደሮች ካምፕ ውስጥ አስሮ እንደበደበ፤ የአካል ስቃይ፣ አስገድዶ የመድፈርና የ4620 .ላይም ግብረስጋዊ ጥቃት እንደፈጸመ ምስክሮች ተናግረዋል።

የመለስ መንግስት ባለስልጣናት የአካባቢ ሚሊሻዎችን ምልመላ በማጣደፍ ያለበቂ ስልጠና ሌሎች የሱማሌ ጎሳዎችን ከኦብነግ ጋር እንዲፋለሙ በማድረጋቸው ከፍተኛ የህይወት ጥፋት ደርሷል።ለመለስ መንግስት የኢኮኖሚ ርዳታ የሚያደርጉለት ለጋሽ ሀገሮች የመለስ መንግስት በአካባቢው የፀረ-ሽብር ጥረት ተባባሪያቸው ቢትሆንም፤ የሰብአዊ መብትን በተመለከተ ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ አልተጫኑም በማለት የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ወቅሷል።
ዋናዎቹ ለጋሽ አገሮች የመለስ መንግስት ላይ ጫና በማድረግ በደሉን እንዲያስቆሙ።የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ቀጥሎ የተዘረዘሩት የመፍትሄ ሃሳቦችን አቅርቧል።

• የአሜሪካ መንግስት በመለስ መንግስት ሰራዊት ስለተፈጸሙ
የመብት ጥሰት
የተጠናቀሩትን ሪፖርቶች እንዲመረምር፤ የመለስ መንግስትም በዚህ ተግባር የተሳተፉ የሰራዊቱን ክፍሎች በመለየት ተጠያቂዎቹን ለፍርድ እስከሚያቀርብ ድረስ፤ አሜሪካ የሰብአዊ መብት ለሚረግጡ የውጭ ሀገር የጦር ሰራዊት ክፍሎች ርዳታ እንዳይሰት በሚከለክለው የ "ሊሂ ህግ"መሰረት ለመለስ መንግስት ምንም አይነት ርዳታና ስልጠና እንዳይሰጥ፤

• የእንግሊዝ መንግስትና የአውሮፓ ህብረት በበኩላቸው በደሉን እንዲያወግዙና ክልሉ እየተፈጸመ ያለውን ወንጀል የመለስ መንግስት እንዲያጣራ በይፋ እንዲያሳስቡና በድርጊቱ የተሳተፉ የሲቪልና ወታደራዊ ባለስልጣኖች በሃላፊነት ይጠየቁ ዘንድ ግፊት እንዲያደርጉ፤

ለልማት ስራ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ለደህንነት ስራ ማስፈጸሚያ መዋሉን እንዲቆጣጠሩ
ጥሪ ያቀርባል።

በደሉ እስከሚቆምና ወንጀለኞቹም ለፍርድ እስከሚቀርቡ ድረስ ለጋሽ ሀገሮች በመለስ መንግስት በኩል ያላቸውን ፖሊሲ እንደገና ሊገመግሙት ይገባል ሲል ድርጅቱ በዘገባው ገልጿል።

ይህ ዘገባ በመንግስቱ ሓይለ ማርያም አስተዳደር ወቅት በጦር ወንጀልና በሰብአዊ ፍጥረት ላይ ተፈጸመ ለተባለ ተመሳሳይ ወንጀል መንግስቱን ጨምሮ በከፍተኛ የደርግ ባለስልጣናት ላይ የመለስ መንግስት የይስሙላ ፍርድ ቤት የሞት ፍርድ በፈረደ ጥቂት ሳምንት መሆኑ ታዛቢዎችን አስገርሟል።ይህን ሁኔታ በእርግጥ መለስና ስርአቱ ከታሪክ የማይማሩ ድኩማን እንደሆኑ አመላካች ነው ሲሉ የሁኔታው ታዛቢዎች ያናገራሉ።እንዳውም መለስና አጋሮቹ የፈጸሙት ተግባር በአለም አቀፍ ማህበረሰቡ በኩል እንዲህ መጋለጡ ለወፊቱ የፍርድ ሁኔታ በር ከፋች እንደሆነና ከስልጣን በሁዋላ የትም ተሸሽገው እንዳይኖሩ በቂ ድጋፍ ማስገኛ እንደሆነ ተናግረዋል።

የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቱ በአለም ላይ ያሉ ጥሰቶችን በመዘገብ የታወቀና የተከበረ ሲሆን በተለይ በ አሜሪካን መንግስት ባለስልጣናትና ተቋማት ዘንድ ተሰሚነት እንዳለው ይታወቃል።ከዚህ ቀደምም ባወጣው የዳርፉርና የቲቤት ዘገባ መነሻነት ከፍተኛ የሆነ አለም አቀፍ እንቅስቃሴና ጫና በመንግስታቱ ላይ እንዲዖርድ እንዳደረገ የሚታዎስ ነው።

## <u>ጀነራሎቹን መደለሉን ተያይዞታል።</u>

ከገጽ 1 የዞረ

በዚህ መንገድ ገንዘብ ተሰጥቶአቸው ከምትሄደው ጀነራሎች አካባቢ ለግንቦት 7 በደረሰን ቀጥተኛ ጥቆማ መሰረት ይህንን ተግባር ከዚህ ቀደም የምታደርገው ቢሆንም ሰሞኑን በስፋት መቀጠሉ የሚያሳየው ሁሉ ነገር አብቅቶለት መለስ ጀነራሎቹን በመለማመጥና በማባበል ለመያዝ የሚያደርገው ሙከራ እንደሆነ ያሳያል በለዋል።ይህ ጀነራሎቹን የመደለል ዘመቻ መለስና አገዛዙ ሁሉንም ነገር በመጠራጠር የመከላከያ ጀነራሎችን በመያዝ በስልጣኑ ለመቆየት የመጨረሻ አማራጭ እንደሆነ አመላካች ነው ሲሉ ይናገርሉ።

በሀገሪቱ ውሰተ ያለው ቀውስ እየተባባሰ መምጣት ያሳሰባቸው አንዳንድ ተመልካቾች ላልተወሰነ ጊዜ የሚቀጥል የሚመስለው የሀገሪቱ ቀውስ ምን አልባት ያልተጠበቀ የመንግስት ለውጥ ያስከትላል የሚለው ስጋት በስርአቱ አካባቢም መሰማቱ ሲነገር የ አዜብ የሰሞኑ ሁኔታም፣ምን አልባት የጦር ጀነራሎች ለመለስ ያላቸውን ታማኝነት እንዲጠብቁ ለማባበል ነው የሚል አስተያየት ሰጥተዋል። ይሁንና ችግሩ ገዛም በላይ እንደገፋና መለስ በጦር ጀነራሎች ድጋፍ ስልጣን ላይ ልቆይ ብሎ ቢያስብ እንኳ ከህዝብ የተቃወሞ አያመልጥም ሲሉ ትንበያቸውን አመልክተዋል።

**አንተ ኩሩ ህዝብ**
**አገርህን አድን !**
**መብትህን አስከብር!**
**ተነስ! ታገል! ተባበር!**